# ፍትህ በእውነትና በማስረጃ ለሚሞግተው ብዕረኛ ተመስገን ደሳለኝ

ፍ-ትህን ናፋቂው ተመስገን በግብሩ

ት-ግሉን ሲያጧጡፈው ታምኖ በብዕሩ

ህ-ዝብ እውነቱ ገባው ወንጀሉን ከስሩ

ለ-ብልቦ ቢፈጃት የአዳነች ግምገማ

ተ-መስገንን አስራ ሚስጥር ስላሰማ

መ-ዛት ጀምራለች ዘራፊዋ ቆማ

ስ-ልጣን ያባለጋት ደፋር ወንጀለኛ

ገ-ናና ዘራፊ አስለቃሽ ቀማኛ

ን-ዴቷ ጥጋቧ አለን አላስተኛ

ፍ-ርድ በእውነት ካለ ትጠየቅ አበቤ

ት-ቢያ ተጭኖበት ቆስሏል አዲስ አቤ

ህ-ያው ወንጀለኛ አነግ አዴፓዋ

ለ-ጥፋት የቆመች ጥጋብ ነው ካባዋ

አ-ርባ ሚሊዮን ብር እንደ ጣፋጭ ልሳ

ዲ-ሞክራሲን ገላ ተመስገንን ከሳ

ስ-ትቆም ልብ ያቆስላል ዘረኝነት ለብሳ

አ-ዳነች አበቤ ከስልጣን ትነሳ

በ-ግምሩክም ቢሆን ወንጀሏ ሲነሳ

ባ-ሳየችው ምግባር ትታሰር ትረሳ

ህ-ዝቡም ሰላም አጣ በእሷ የተነሳ

ዝ-ንት አለም አትኖሩም ይህን አለም ያውቃል

ብ-ትወዱም ብትጠሉ ተረኝነት ያልቃል።

ዘውዲቱ የማነ

2020-10-14